# የካቲት 12--የሰማዕታት ቀን፡ መዘከር ብቻ ሳይሆን በተራም መታገል

ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ

ከዓመት ዓመት ኢትዮጰያውያን የካቲተ 12ን የሰማዕታት ቀን ብለው የሚያከብሩት በየካቲ ት12 የጣሊያኑን ወራሪ ማርሻል ሺከቶር ሩዶልፎ ግራዚያኒ ላይ በአዲስ አበባ በገነተ ልዑል (ትንሹ ግቢ) የግድያ ሙከራ ከደረሰበት በኋላ በዚያ ቀንና በቀጣይ ሁለት ቀናት በጣሊያኑ ባለስልጣን በግዊዶ ኮርቴሴ በተሰጠ ትዕዛዝ መሰረት ከ 30 ሺ በላይ ዜጎች በአሰቃቂ ሁኔታ በአዲስ አበባ ተጨፈጭፈው አልቀዋል:: በሙሶሊኒ ዕዝም መሰረት የጥቁር አንበሳ አርበኞና የነበሩ ጥቂቶች ኢትዮጵያ ምሁራንም ታድነው ሲገደሉ፣ ለጥቆም በደብረ ሊባኖስ ከመቶ በላይ ቄሶች፣ ካህናትና ባሕታውያንም ተረሸነዋል::

የካቲተ 12 በኢትዮጵያ ታሪክ አሰቃቂ ምዕራፍ ነው:: በርግጥ በደርግም በወያኔም ብዙ የሕዝብ ፍጅቶች ታይተው በሩቅ ርቀት ሳይሆን በቅርቡ ቀይ ሽብር፣ ወተር፣ አርባጉጉ፣ ጋምቤላ፣ አጋዴን፣ አሶሳ በደኖ ፣ ወዘተ በሚለው እንድናተኮር ማድረጋቸውን እናውቃለን:: የግራዚያኒና የፋሽስቶቹ ግፍና ጭፍጨፋ ከቶም የሚረሳ አይደለም:: ለዚህም ነው ዜጎች ለግራዚያኒ በጣሊያን ሐውልት ሲቆምለት የተቃወሙት:: ለዚህም ነው የጣሊያን መሪ የነበ ረው ቤርሉስኮኒ የሙሶሊኒ አገዛዝ የተወረሩትን ሕዝቦች ጠቀመ ሲል አጥብቀን የምንቃውመ ው:: ለዚህም ነው ኢሕአፓም ሌሎችም ለሙሶሊኒ ወራሪ ጦር ወርቅም፣ ድጋፍም፣ ቡራኬ ም የሰጠችው የካቶሊክ ቫቲካን ተቋም--ለአይሁዶች ይቅርታ እንዳለችው ሁሉ-- ዛሬ የኢት ዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ አለባት የሚሉት:: ታሪክና ሀቅ ተደብቆ ወይም ተረስቶ አ ይቀርምና ኢትዮጵያውያን ከዓመት ወደ ዓመት የካቲት 12ን ያከብራሉ፣ ይዘክራሉ:: ዝክሩ የደረሰውን ለመዘከርናና ሀገር እንዴትም እንደተጠበቀችም ለማስታወስ ነው::

ዝክር ካልን ዘንዳ የነበረውን ማስታወስ የግድ ነው:: የናፖሊ ኢጣሊያ ልዑል ተወለደ በሚል ግራዚያኒ በቤተ መንግስት በዓል አድርጌ ለለማኞችም እኔው ለጋሽ ልሁን ይላል:: ብዙዎች ይሰባሳበሉ--የጣሊያን ባለስልጣኖች፣ ባንዳዎች፣ የእኔ ብጤዎች ወዘተ ... :: ለዚሁ በዓል ደግሞ ሞገስ አስጌዶምና አብርሃም ደቦጭ የተባሉ ወጣቶች -- በዛሬው ክልላዊ መለያ ደግሞ ኤርትራውያኖች - ይዘጋጃሉ:: የሚወረውሩትን ከአስር በላይ ፈንጂ ቦምቦች አቅራ ቢው ደግሞ ታክሲ ነጂው ስምዖን አደፍርስ ይባላል:: ሞገስና አስጌዶም ተሽለኩልከው ገብተው ከ 10 በላይ ቦምብ በግራዚያና ላይ ይወረውራሉ:: ግራዚያኒ ባይሞትም በ 365 ፍንጣቂ ተመቶና ቆስሎ ወደ ሆስፒታል ይወሰዳል:: የአቡነ ቄሬሎስ ሹፌር ሲሞት አቡኑ

ይቆስላሉ፡፡ ጄኔራል አርማንዶ ፔትሪትና የጣሊያን አየር ኃይል አዛዥ በኢትዮጵያ (የመርዝ
ጢስ አሰረጪው) ጄኔራል ሊዮታም ይቆስላሉ -- ሊዮታ እግሩ ይቆረጣል፡፡ በዚህ የተነሳም
የጣሊያን ወራሪ ጦር ፍጅቱን በአዲስ አበባ፣ ደብረ ሊባኖስ ወዘተ አካሂዶ ከ 30 ሺ ያላነሱ
ኢትዮጵያውያንን ይፈጃል፡፡ የጣሊያን ጦር ባንዳዎችንም ሆነ ቦምብ ወረሩ ብሎ ያጋለጠው
ንም ከህዲ አየለ ጉባዔንም ሳይቀር ለእስር ይዳርጋል፡፡ ወታደራዊ ፍርድ ቤት አቆመኩ ብሎ
ም ብዙዎች ላይ ፍርደ ገምድሉን አሳልፎ ረሽኗል፡፡ በዜጎች ሬሳ ላይ ሲያሾፍ የተነሳው
በርካታ ፎቶም እስከዛሬ አለ፡፡

የካቲት 12ን ስንዘከር መገንዘብ ማማር ያሉብን ሀቆች አሉ፡፡ በተለይም ዛሬ ትግልና መስዋዕ
ትነት መጨረሰና ማስጨረስ ብለው ለሚያላዝኑ ክፍሎች፣ እነ አብረሀምና ሞገስ ተማሩ ይላ
ሉ፡፡

- በቅድሚያ ጀግኖቹ በውልደት ኤርትራዊ ቢሆኑም ሀገራችን ኢትዮጵያ ብለው ለመስ
  ዋዕትነት መዘጋጀታቸው ዛሬ ማንነታቸወን ለካዱ ሁሉ ትምህርት ነው፡፡
- በግራዚያኒ ላይ የግድያ ሙከራ ማድረጋቸው ጀግና አሰኝቶ እስካዛሬ የሚያስደንቃቸ
  ው ናቸው እንጂ ያውም ሳይገሉት ሕዝብን አሰጨረሱ ብሎ የሚያስወግዛቸው አይደ ለም
  ፣ አልሆነም፡፡ የዛሬ ጥራዝ ነጠቅና አልፎም ቡከን ፖለቲከኞች በትግል የተሰዉትን ከን
  ቱ፣ የታገሉትን አስጨራሽ ለሚሉት የካቲት 12 ማፈሪያዎች ይላቸዋል፡፡ ሁለት ግለሰ
  ቦች በወረወሩት ቦምቦች (ግራዚያኒ ባይሞትም ) ከ30 ሺ ያላነሰ ዜጋ ተረሽኗል፣ ተገ
  ድሏል፡፡ አስጨረሱ ሕዝብን እነ አብርሃምና ሞገስ?

ጀግኖቹ ወደ ሱዳን ሊሸሹ ሲሉም የገደላቸው ጣሊያን ሳይሆን የጎጃም አርሶ አደር ነው፡፡
ተጠቅተው የሚያፈግፍጉ አርበኞችንም ከወሎ ጎጃም እስከ ጂማ ወዘተ ሀገሬው መግድሉ
ምስጢር አይደለም፡፡ ይህም ሌላ ሽክማችንና ማፌሪያችን ሆኖ የቀጠለ ነው፡፡ የኢሕአ
ፓ ታጋዮች በአርሶ አደር ላይ አንተኩስም ብለው ግን በነዚሁ ተይዘው ለደርግ ተሰጥተ
ው፣ ወርቅ ታጋዮች ለሞት በቅተዋል፡፡ አርበኞችንም ከጅማ እስከ ሲዳማ ና ወሎም ወገን
አጥቅቶና ለጣሊያንም አሳልፎ ሰጥቶ ማስገደሉ ታሪካችን ነው፡፡ የካቲትም ይህን ያስተ
ምራል፡፡ እወቁት ተቀበሉት፣በጋራም እንፈርበት፣ አይደገም ይላል፡፡ የባንዳው መንጋ
ብዙ ነበረ፣ ለጣሊያን ያደረውም ጥቂት አልነበረም ፡፡ ዛሬም በወያኔ ጊዜ እየታየ ያለ ነ
ው፡፡ ለዚህም ነው ከየካቲት 12 መማር ያለብን -- ዛሬም እውነታችን ነውና፡፡ ፍርሀቱ
ም ከህደቱም አለ፡፡ ወኔ ቢያጥጥም ድራሹ አልጠፋም፡፡ በጣሊያን ጊዜ የተፈጀው ጀ
ግና ምሁርና በደርግ ጊዜም ሞት አይፈሬ ሆኖ የታገለው ተራማጅ ግን ዛሬ በአሳዛኞችና
የባዕድ ቅጥረኞች ሚናውና ግዳጁ ተክዶ መገኘቱ የሚሸፋፈን አይደለም፡፡

የካቲት 12 የጀግኖች ቀን፤ የሰማዕት ቀን። ትግል የሚጠይቀው መስዋዕትነት የተከፈለ
በት ጊዜ። አስፈጃችሁን ያለ አልነበረም፤ ዛሬም የለም - ከውጉዞቹ በታሪክ ተጠያቂዎች
በስተቀር። ይህን አልገነዘብ ብለው ሰማዕትን የሚያጥላሉ ዛሬም ሆነ ትላንት ለኢትዮጵ
ያ ሲሉ መስዋዕትነት የከፈሉትን ሊያወግዙ ቀርቶ ሊተቹ ብቃትና መሰረት አንደሌላቸ
ው ማወቅ አለባቸው። የሀገር ነፃነትና ክብር በወሬ ሳይሆን የሚከበረው በመስዋዕትነትና
በትግል ነው። የፊሪ ተለይ፤ የባንዳ ራቅ ነጋሪትም የሚጎሰመው ለዚህ ነው።

ለኢትዮጵያ የተሰዉት ሰማዕት ሁሉ ክቡርና ሕያው ናቸው!!
ለሀገርና ለወገን እንታገል፤ ሞት አይፈሬም እንሁን!!